የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት
ETHIOPIAN CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS COUNCIL

USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

# የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ላይ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የተሰበሰበውን ግብዓት መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ የፖሊሲ አጭር መግለጫ

## በኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት የተዘጋጀ

ግንቦት 2015 ዓ.ም.

**አዲስ አበባ**

Feteh (Justice) Activity
IN ETHIOPIA

ይህ ህትመት በዩ ኤስ አሜሪካ ዓለምአቀፍ የልማት ኤጀንሲ (ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ) በአሜሪካ ህዝብ ድጋፍ በኩል ማከናወን ተችሏል፡፡ በሰነዱ የተገለጸ ይዘት እና ሀሳብ/አማካከት በማንኛውምመንገድ የዩ ኤስ አሜሪካ ዓለምአቀፍ የልማት ኤጀንሲ አማካከትን አያንጸባርቅም፡

## ማውጫ

1. አህጽሮተ ማጠቃለያ ..... 3
2. የአጭር ፖሊሲ መግለጫው ዳራ ..... 3
3. የዚህ የፖሊሲ መግለጫ ዓላማዎች ..... 4
4. ሥነዘዴና አቀራረብ ..... 4
5. ለሽግግር ፍትህ አጠቃላይ ቅድመ-ሁኔታዎች ..... 5
5.1. ሽግግር ..... 6
5.2. የፖለቲካ ቁርጠኝነት ..... 7
5.3. ተዓማኒነት ..... 7
5.4. አካታችነት ..... 8
5.5. የስርዓተ-ጾታ ፍትህ ..... 8
5.6. ተጋላጭ የማህረሰብ ክፍሎች ..... 9
5.7. በሽግግር ፍትህ ሂደት የሚካተቱ ግጭቶችን የመለያ መርሆዎች ..... 9
6. የሽግግር ፍትህ ዋናዋና ተዋናዮች ..... 10
6.1. ኮሚሽኖችና የፍትህ ተቋማት ..... 10
6.2. መንግስት ..... 11
6.3. የፖለቲካ ፓርቲዎችና መንግስታዊ ያልሆኑ ተዋናዮች ..... 11
6.4. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ..... 12
6.5. የአገር በቀል ዕውቀቶችን መጠቀም ..... 12
7. የሽግግር ፍትህ የሚሸፍነው የጊዜ ወሰን- *ከሰሜኑ ጦርነት ጀምሮ ወይስ በማንኛውም ጊዜ የተከሰቱ ግጭቶችን ባካተተ መልኩ* ..... 13
8. ፌዴራሊዝምና ሕገመንግስታዊ ጉዳዮች ..... 14
9. ተቋማዊ ማሻሻያ ..... 15
10. የሽግግር ፍትህ ዓለምአቀፋዊነትና የንጽጽር መለኪያ ..... 15
11. የሽግግር ፍትህ አማራጮች ..... 17
11.1. እውነትን ማፈላለግ ..... 17
11.2. ማካካሻ ..... 17
11.3. ክስ ..... 18
11.4. ምህረት ..... 19
11.5. ፖሊሲ አማራጭና አተገባበሩን በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች ..... 19
12. የማጠቃለያ ምክረ ሀሳቦች ..... 19
12.1. ማጠቃላያ ..... 19
12.2. አጠቃላይ ምክረ ሀሳቦች ..... 20

## 1. አህጽሮተ ማጠቃላያ

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በሲቪል ማህበራት አዋጅ ቁጥር 1113/2019 አንቀጽ 85 መሰረት በታህሳስ ወር 2012 ዓ.ም በህግ የተቋቋመ ድርጅት ነው። ምክር ቤቱ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን (ACSO) የተመዘገቡ ከ4500 በላይ የሚሆኑ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን፣ ማህበራትን እና ህብረቶችን የሚወክል ከፍተኛ አካል ነው። ምክር ቤቱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅትን የመወከል እና የማስተባበር ሀላፊነት በህግ ተሰጥቶታል፡፡ ምክር ቤቱ የሚተዳደረው በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ሁሉም የሲቪል ማህበራት ሙሉ ተሳትፎ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ነጻ የሆነ ተቋም ሆኖ ይሰራል። ምክር ቤቱ ዘርፉን በመደገፍ፤ በማስተባበርና በመወከል የሲቪል ማህበራትን ራስን በራስ ቁጥጥር ስርዓትን በመዘርጋትና በማስፈጸም፡ የእውቀት ምርትና ስርጭት፤ የፖሊሲ እና የቁጥጥር ማሻሻያዎችን በመምራት; በሲቪል ማህበረሰብ ጉዳዮች ላይ ባለስልጠን መ/ቤቱን፤ መንግስት እና ሌሎች ሴክተሮችን በማማከር; የዘርፉን ምህዳር ጥበቃ በማጠናከር፤ መልካም ገጽታ በመገንባትና ትስስርን በማጠናከር ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዘርፍ እድገት ሁለገብ ሚናዎችን ይጫወታል።

ምክር ቤቱ ከዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ፍትህ (ጀስቲስ) ተግባራት በኢትዮጵያ ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ ይህንን የፖሊሲ አጭር መግለጫ በማዘጋጀት የኢትዮጵያ የሽግግር የፍትህ ፖሊሲ ውስጥ በሚካተቱት የሽግግር የፍትህ ፖሊሲ አማራጮች ላይ ግብአት በማቅረብ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ ጥረት አድርጓል፡፡ በዚህ አውድ ውስጥ ይህ የፖሊሲ ማጠቃለያ ከሲቪል ማህበረሰብ ሴክተር በተሰበሰበው ግብአት ላይ ተመርኩዞ የተዘጋጀ ሲሆን ከተለያዩ ክልሎች የተውጣጡ የሲቪል ማህበራት በአራት የምክክር ፣ በአንድ የማረጋገጫ አውደ ጥናት እና በበይነ መረብ ላይ ሃሳባቸውን ለመሰብሰብ ታስቦበተዘጋጁ መድረኮች ላይ በመሳተፍ ሀሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡ በእነዚህ አውደ ጥናቶች እና የበይነመረብ መድረኮች ላይ 285 የሲቪል ማህበረሰብ ድርቶች ተሳትፈው በሽግግር የፍትህ ፖሊሲ አማራጮች ሰነድ ላይ አስተያየትና ግብዓት ሰጥተዋል። ይህ አጭር የፖሊሲ መግለጫ በምክክሩ ወቅት በሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች ላይ በተሳታፊዎች የተሰጡ ዋናዋና አስተያየቶችን በመዘርዘር አጠቃላይ ግኝቶች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ አያይዞም የሲቪል ማህበራት ሊኖራቸው የሚችለውን ጉልህ ሚና ይዘረዝራል። መግለጫው በአጭር በአጭሩ የተደራጁ ዋና ዋና፤ እንዲሁም ንዑሳን ክፍሎች ያሉት ሲሆን ዓላማዎቹን በመዘርዘር ጀምሮ አስተያየቶችና ምክረሀሳቦን በመስጠት ይጨርሳል፡፡ በእያንዳንዱ ዋና እና ንዑስ ክፍል ስር ከተሰጡት የተወሰኑ ምክረሀሳቦች በተጨማሪ፣ በዋናነት በቀጣይ በሚወጣው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸውን አማራጮች፤ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የተለያዩ ተግዳሮቶችን እንዲሁም የፖሊሲ ዕቅድ እና ትግበራ ላይ ምክረሀሳቦችን ይሰጣል።

## 2. የአጭር ፖሊሲ መግለጫው ዳራ

የፍትህ ሚኒስቴር በስሩ ያዋቀረው ብሄራዊ ግብረሃይል በሽግግር ፍትህ ላይ መጠነ ሰፊ ጥናት በማድረግ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች የያዘ ሰነድ አዘጋጅቶ በጥር ወር 2015 ዓ.ም ግብዓት ለመሰብሰብ ለውይይት አቅርቧል፡፡[1] ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በፌዴራል፣ በክልል እና በአካባቢ ደረጃ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ግብዓት ለማሰባሰብ ተከታታይ ምክክር እየተካሄደ ይገኛል። ይሁን እንጂ በሰነዱ ዝግጅት ወቅትም ሆነ ከዚያ በኋላ ባለው ሂደት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተቀናጀ መልኩ ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ እድል አልተሰጣቸውም፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ቀረጻ ላይ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ምክር ቤት ተነሳሽነቱን

[1] ኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ከባለድርሻ አካላት ግብአት ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ጥር 2015 ዓ.ም. አዲስ አበባ

በመውሰድ ምክር ቤቱ ከዩ ኤስ ኤ አይ ፍትህ (ጀስቲስ) ተግባራት በኢትዮጵያ ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ በርካታ ከፍተኛ የምክክር ስብሰባዎችን በማዘጋጀት ይህንን የፖሊሲ አጭር መግለጫ አዘጋጅቷል[2]፡፡

በአጠቃላይ ይህን የፖሊሲ አጭር መግለጫ በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ የሲቪል ማህበራት ባለሙያዎች እና መሪዎቻቸው ተሳትፎ እጅግ አስደናቂ ነበር፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ለእውነተኛ ሰላምና ዲሞክራሲ ሽግግር በሚደረገው የፖሊሲ እቅድ ዝግጅት፣ አፈፃፀም እና በአጠቃላይ ለሽግግር ፍትሁ ስኬት ያላቸውን ፍላጎት፣ ቁርጠኝነት እና ከፍተኛ አቅም አሳይቷል። የውይይት መድረኮቹ ከግብዓት ማሰባሰቢያነት በተጨማሪም በአጠቃላይ በሽግግር ፍትህ ምንነት፣ ይዘት እና ስኬት በተለይም የመንግስት የባለቤትነት እና የሲቪክ ማህበራት አዎንታዊ ሚና፣ ለፖሊሲ ትግበራ ሁኔታዎችን የማመቻቸት አስፈላጊነት እና የመሳሰሉት፤ በተለይም በኢትዮጵያ ሁኔታ የሽግግር ፍትህ አስፈላጊነት ላይ ግንዛቤ የማስጨበጥ እድል ፈጥረዋል፡፡የዚህን መግለጫ ረቂቅ ትክክለኛነት ለማረጋገጥም በመጨረሻው የማጠናከሪያ አውደ ጥናት ላይ ለውይይት ቀርቦ የመጨረሻ ቅርፁን እንዲይዝ ተደርጓል።

## 3. የዚህ የፖሊሲ መግለጫ ዓላማዎች

የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች ሰነድ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የሰነዱ ዓላማ በቀጣይ ለሚዘጋጀው ፖሊሲ አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን ለመሰብሰብ ያለመ ነው፡፡ ይህን ግብ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሚና ጋር በማጣጣም ይህ አጭር የፖሊሲ መግለጫ የሚከተሉትን አላማዎች አስቀምጧል።

- በተዘጋጀው የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች ሰነድ ይዘት ላይ መወያየትና ምክረሀሳብ ማቅረብ፤ እንዲሁም በቀጣይ ለሚዘጋጀው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ከሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ግብዓቶችን ማሰባሰብ፤
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በቀጣይ በሚዘጋጀው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት እንዲሁም ትግበራ ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን እምቅ አቅም መለየት፤ እንዲሁም፣
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አመራሮችና ባለሙያዎች በሽግግር ፍትህ ምንነትና እና አስፈላጊነት ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ማዳበር ናቸው፡፡

## 4. ሥነዘዴና አቀራረብ

ከላይ ከተጠቀሱት ዓላማዎችን ታሳቢ በማድረግ፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ግብአቶችን ለመሰብሰብ ሁለት አይነት መድረኮችን አዘጋጅቷል። የመጀመሪያው ፊት ለፊት የሚደረጉ የምክክር አውደ ጥናት መድረኮች ሲሆን ሁለተኛው ዲጂታል ቴክኖሎጅን በመጠቀም በጎግል ፎርም በቀጥታ በበይነ መረብ የተዘጋጀ መድረክ ሲሆን ይህም ከሲቪል ማህበራት የሚመጡ ግብአቶችን ማሰባሰብን ኢላማ ያደረገ ነው።


ይህን ዓላማ ለማሳካት በሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች ሰነድ ላይ በቅድሚያ ከተለያዩ ተቋማት ከተውጣጡ ባለሙያዎች ጋር አንድ ከፍተኛ ምክክር (በአዲስ አበባ) እንዲሁም ከተለያዩ የሲቪል ማህብረሰብ ድርጅቶች አመራሮችና ባለሙያዎች ጋር አራት የምክክር ስብሰባዎች (በአዲስ አበባ፣ ደሴ እና ሰመራ) በማካሄድ ግብአቶችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በሁሉም የምክክር ስብሰባዎች ላይ በፍትህ ሚ/ር የተዘጋጀው ሰነድ በተሟላ መልኩ ለውይይት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በሂደቱም ተሳታፊዎች በሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች አላማዎች፣ ይዘት፣ ቅርፅ፣ እና ተያያዥ የፖሊሲ አማራጭ ጉዳዮች ላይ፤ እንዲሁም የህዝብና ሲቪል ማህበራት የተሳትፎ መንገዶች ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ሰፊ


[2] አንድ የምክክር መድረክ ከባለሙያዎች ጋር በቀን ሚያዚያ 18/2015 ዓ.ም. በአዲስ አበባ የተደረገ ሲሆን በመድረኩ ላይ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ሰነድ ካዘጋጁት ባለሙያ አንዱ ሰነዱን አቅርበዋል። በተጨማሪም ሁለት የምክክር መድረኮች በቀን ግንቦት 1/2015 ዓ.ም. በአዲስ አበባ እንዲሁም በክልልም በቀን ግንቦት 7/2015 ዓ.ም. በደሴና በሰመራ ከሲ.ማ.ድ ጋር ምክክር ተደርጓል።

ውይይት ለማድረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ም/ቤት ሰነዱን መሠረት በማድረግ ዝርዝር ጥያቄዎችን በማዘጋጀት በእያንዳንዱ የምክክር መድረክ ላይ የተሳተፉ ሁሉ መጠይቆቹን እንዲሞሉ ያደረገ ሲሆን፤ በኦንላይን (Google ቅፅ)[3] ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡ በመጠየቅ መረጃ ለመሰብሰብ ችሏል። በዚህም መሠረት፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ካውንስል በምክክር ስብሰባዎቹ መድረክ የተገኙትን ግብዓቶች እና በመጠይቆቹ የተሰበሰቡትን አስተያየቶች በአግባቡ በመቀመርና በመተንተን ይህን የፖሊሲ አጭር መግለጫ አዘጋጅቷል፡፡

የእነዚህ የከፍተኛ ደረጃ የምክክር ስብሰባዎች እና የኦንላይን መድረኮች ተሳታፊዎች በልማት፣ በሰላም ግንባታ፣ በዴሞክራሲ፣ በጾታ እና አካቶነት (በአካል ጉዳተኞች ወይም በአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ላይ ያተኮረ) እና በሰብአዊ መብት ተግባራት ላይ የተሰማሩ ዋና ዋና የሲቪል ማህበራት ነበሩ። ምክር ቤቱ የተሳታፊዎችን ዝርዝር በሚየዘጋጅበት ወቅት በተጋላጭ ቡድኖች ላይ የሚሰሩ የሲቪል ማህበራት በልዩ ትኩረት እነዲካተቱ በማድረግና ዝርዝሩ ጥሪ ከመተላለፉ በፊት በፍትህ ቡድን *(Feteh's team)* በቅድሚየ እንዲታይ በማድረግ በተለይ በተጋላጭ ቡድኖች ላይ የሚሰሩ የሲቪል ማህበራት ተሳትፎን አረጋግጧል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በአካል የምክክር አውደጥናት መድረኮች ላይ ከተገኙ 160 የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች (96 ከክልሎች የተውጣጡ) እንዲሁም በበይነ መረብ በተዘጋጀው የጎግል ፎረም መድረክ ላይ ሀሳብ ከሰጡ 125 የሲቪል ማህበራት ተጨማሪ ሀሳቦችና ግብዓቶችን ተቀብሏል። በአጠቃላይ ከ285 የሲቪል ማህበራት ግብዓት የተሰበሰበ ሲሆን ይህም ከሁለት ከተማ አስተዳደሮች (ከአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ) እና ከአምስት ክልሎች ማለትም አማራ፣ አፋር፣ ሶማሌ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ኦሮሚያ፣ ትግራይ እና ጋምቤላ ክልሎች የተሰበሰበ ነው፡፡




የሚቀጥሉት ክፍሎች በክፍል እና በንዑስ ክፍል በተዘጋጀው የፖሊሲ አማራጭ ሰነድ ላይ በተዘረዘረው ጽንሰ ሃሳብ ላይ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት የተሰጡትን ግብአቶችንና ሃሳቦችን ያሳያሉ። በእያንዳንዱ ክፍል እና ንዑስ ክፍል ስር የተወሰኑ ምክረ ሀሳቦችም ቀርበዋል፡፡

## 5. ለሽግግር ፍትህ አጠቃላይ ቅድመ-ሁኔታዎች

በኢትዮጵያ ጥሩ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ ለመንደፍ እንዲሁም በተሳካ ሁኔታ መፈጸሙን ለማረጋገጥ በርካታ ቅድመ ሁኔታዎች ተቀምጠዋል። በምክክር መድረኮቹ ትኩረት ከተሰጣቸው ዋና ዋና ቅድመ ሁኔታዎች መካከል፡- የፖለቲካ ሽግግሩ መደላድል፣ የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣ ተአማኒነት፣ አካታችነት፣

[3] በም/ቤቱ ድህረ ገፅ ላይ የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች ሰነድ በhttp://ecsoc.net/index.php/ecsoc-resources እና የጎግል ግባዓት ማሰባሰቢያ ቅፅ በhttp://forms.gle/BvFncPFutqpbPEET9

የሥርዓት-ፆታ ፍትህ፣ ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎችን ማካተት እና (የተቋም መሪዎችን) የመምረጫ ሂደት መርሆዎች ናቸው።

### 5.1. ሽግግር

የሽግግር ፍትሕ የእርስበርስ ግጭትን፣ ጭቆና እና ግዙፍ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በመፍታት፣ ፍትህንና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ፣ ሰላም፣ እርቅ እና ዲሞክራሲን ለማረጋገጥ የሚደረግ ሂደት ነው፡፡ ይህን እምቅ የለውጥ ሃይል አካሄድ የሚደግፉ ተከታታይ ሂደቶችንና ዘዴዎችን ያካታቱ መሰረታዊ ግምቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ ግምቶች አንዱ ሽግግርን የሚመለከተውና ከፈላጭ ቆራጭነት ወደ ዴሞክራሲ፣ ከግጭት ወደ ሰላም፣ ከመብት ረገጣ ይልቅ የመብት መከበር ወደሚረጋገጥበት ሥርዓት፣ ወዘተ ለመሸጋገር አስቻይ ሁኔታ አለ የሚለው ግምት ነው። ነገር ግን ሽግግር እንዲኖር የሚስችሉ ሁኔታዎች እሴቶች፣ ቁርጠኝነት፣ የተቋማት አደረጃጀት እና የመሳሰሉት አሁን በኢትዮጵያ አሉ ወይ የሚለው ቁልፍ ጥያቄ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በግጭት ውስጥ መቆየቷ ያስከተለው ጫና እና የሰላም አስፈላጊነት የማይካዱ እውነታዎች ቢሆኑም ወደ ዘላቂ ሰላም፣ የማኅበረሰቦች መቻቻልና መከባበር፣ ዴሞክራሲ፣ ልማት፣ ጠንካራ ተቋማት መመስረት ወዘተ. መሠረት ለመጣል የሚደረግ ጉልህ የሽግግር ቁርጠኝነት ላይ መሆኗን በማሳየት ረገድ ግን አሁንም ቀሪ ሥራዎች እንዳሉ ይታመናል፡፡ የሽግግር ሂደት ፍትህ የሚሰጥበትን መንገድ መዘርጋት እና ማህበረሰቡ ተመልሶ ወደቀደመው የግጭት ሁኔታ እንዳይመለስ ለማድረግ የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፤ በመጨረሻም ዘላቂ ሰላም፡ እርቅ፡ መረጋጋት እና የህግ የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት ለመገንባት የሚቻልበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሚያሰጋው፣ በሀገራችን ኢትዮጵያ ከፖለቲካ ንግግሮች እና ተራ የቃል ወይም የጽሁፍ መግለጫዎች በስተቀር መንግስት የሽግግር ፍትህ ሂደትን ለማከናወን የሚያስችል ሽግግር ላይ ነው ወይ የሚለው ትኩረት የሚስብ ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ማለት ለሽግግር ዝግጁነት ከሌለ የሽግግር ፍትህ የመሳካት እድሉ አጠራጣሪ ይሆናል ማለት ነው። አስቻይ ሁኔታዎች በሌሉበት ሁኔታ ሁሉንአቀፍ የሽግግር ፍትህ አላማዎችን ለመተግበር መሞከር ካልተሳካ ውድቀቱ ከፍተኛ አሉታዊ ውጤት ሊኖረው ይችላል፡፡ ስለሆነም ከእውነታ የራቁ ተስፋዎችን በመቀነስ ሽግግራዊ መዋቅሮችን ማጠናከር ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። በዚህ ረገድ በሽግግር ፍትህ ዕቅድ ውስጥ ሊነሱ እና መፍትሄ ሊያገኙ ከሚገባቸው ጥያቄዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- የመጀመሪያው የሽግግር ፍትህ ስርዓትን ለመተግበር ወደሚያስችል ሽግግር ተካሂዷል ወይ የሚለው ነው፡፡
- ዲሞክራሲና የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መሠረታዊ የሰላምና ጸጥታ ሁኔታዎች በሌሉበት እንዴት የሽግግር ፍትህ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል የሚለው ሌላው ጥያቄ ነው፡፡
- በአጠቃላይ አሁንም ግጭት ውስጥ ወይም ጅምላ የሰብዓዊ መብት ረገጣ እና ጭካኔ በሞላበት ሁኔታ ውስጥ ሆነን እንዴት የሽግግር ፍትህ ሊተገበር ይችላል የሚለው ጥያቄ ዋነኛው ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

የተሰጡት ምክረሀሳቦች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- በኢትዮጵያ እውነተኛ የሽግግር ፍትህን ለመተግበር የሚያስችል አገራዊ ሁኔታ ላይ ምልከታ የሚያደርግ ጥናት ባስቸኳይ መካሄድ አለበት።

- የሽግግር ፍትህ ሂደትን ለማናወን የሚያስችል ሁኔታ አለ ከተባለም እንኳን ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለመቀነስ ባለድርሻ አካላትን የማሳመን፣ ወደቀደመው የግጭት ሁኔታ እንዳይገባ ስለሰብዓዊ መብት መከበርና ስለተበደሉ ዜጎች መሚገት ወይም ሌሎች ሰላማዊ የሽግግር መንገዶችን በመጠቀም የተሟላ ሽግግርን የማምጣት ጥረት መደረግ አለበት።
- የሽግግር ፍትህ ሂደትን ለማከናወን እንደ አንድ አስቸኳይ የፖሊሲ ዝግጅት ጉዳይ መንግስት የህግ የበላይነትን በማክበርና በማስከበር የሰው ልጅ ደህንነትን ማረጋገጥ አለበት።

## 5.2. የፖለቲካ ቁርጠኝነት

እንደሚታወቀው በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ውስጥ በመደበኛነት ከሚገለፁ ጉዳዮች ውስጥ ሰላምን ማስፈን፣ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣ እውነትን መፈለግ፣ ካሳ እና ዕርቅ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ማከናወን የመሳሰሉት ተደጋግመው ይነሳሉ፡፡ ነገር ግን ሽግግሩ የተሳካ እንዲሆን የፖለቲካ ቁርጠኝነት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ቁርጠኝነት በተግባር እና በውጤት የሚገለጽ እንጂ የፖሊሲ ሰነዶችን በማዘጋጀት ወይም መግለጫዎችን በመስጠት ብቻ የሚረጋገጥ አለመሆኑም አብሮ መታወቅ አለበት። በዚህ ጉዳይ ላይ ዜጎችን እና በሰላም እና በዲሞክራሲ ግንባታ ላይ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላትን ሊያስጨንቁ የሚችሉ አንዳንድ ድርጊቶች እና ዝምታዎች አሉ። ለምሳሌ በቅርቡ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል በፕሪቶርያ የተከናወነውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ የተካሄደው 'የሽልማት ሥነ-ሥርዓት' በሚሊዮን ለሚቆጠሩ እና በጦርነቱ ሰለባ ለሆኑት ወገኖች ዕውቅና አይሰጥም። በተጨማሪም በዚህ ጉዳይ ላይ በምክክር መድረኮቹ ከተነሱት ውስጥ የተወሰኑት የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

- በቅድሚያ በፕሪቶሪያው የሰላም ሂደት፣ ስምምነት እና አተገባበር ላይ ግልጽነት አልታየም፤ በተለይም ሁለቱ የስምምነቱ ተዋናዮች ተጎጂዎችን ይቅርታ አልጠየቁም። በተጨማሪም ከሁለቱም ወገኖች የተውጣጡት ባለስልጣናት ለጊዜውም ቢሆን ከጭካኔ እና ከሰብዓዊ መብት ረገጣ ተጠያቂነት ነፃ ሆነው ይታያሉ፤ እንዲያውም በእነዚህ ወንጀሎች የተሳተፉ ባለስልጣናት ከፍ ከፍ እየተደረጉ እና እየተሾሙ ነው የሚል ትችት ቀርቧል፡፡ እነዚህ ለሽግግር ፍትህ መሳካት የቁርጠኝነት ምልክቶች አይደሉም።

ስለሆነም እስካሁን የተከናወኑ ሂደቶች ማስተካከያ ካልተደረገባቸው በቀጣይነት የሚዘጋጀው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እና የሽግግር ፍትህ ሂደቶች ዓለም አቀፍ ጫናዎችን ለመመከት የታቀዱ ትርዒቶች ወይም ታክቲካል ፖሊሲ ሆነው ይቀጥላሉ የሚል ስጋት በባለድርሻ አካላት ዘንድ አሳድሯል።

የተሰጡት ምክረሀሳቦች የሚከተሉትን ያካትታሉ፤

- የሽግግር ፍትህን ለመተግበር በሚከናወኑ ሂደቶች የመንግሥት ቁርጠኝነት የፖሊሲ ሰነድ በማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን በአግባቡ በመተግበርም ጭምር መረጋገጥ ይኖርበታል፤
- መንግስት ወደፊት በሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ ሊታዩ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ አስቀድሞ ተጽዕኖ ከሚፈጥሩ ድርጊቶች መቆጠብ ይኖርበታል።
- መጠነሰፊ የመብት ጥሰቶች እና በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ውስጥ ተሳትፎ እንዳላቸው የሚጠረጠሩ ባለስልጣናት እና ግለሰቦች በምንም መልኩ ወደሹመት ወይም ከፍተኛ የደረጃ እድገት ሊደረግላቸው አይገባም።

## 5.3. ተዓማኒነት

የሽግግር ፍትህ ሂደት ተገቢነት ያላቸውን የሽግግር ፍትህ አላባዎችን በአንድነትና በተመጋጋቢነት ያካተተ ሁለንተናዊ አካሄድ ነው። አተገባበርና ውጤታማነት በማበህረሰቡ ድጋፍና ዕምነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ስለሆነም የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አዘገጃጀትና ተግባራዊነት (አፈጻጸም) በማህረሰቡ ዘንድ ቅቡልነት እና ተዓማኒነት ሊያገኝ ይገባል፡፡ በማህበረሱ ዘንድ ተአማኒነት ባላገኘበት ሁኔታ ግን

የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ማስረጃ በማሰባሰብ እና እውነትን በማግኘት፣ በጅምላ ውይይቶች፣ በማኅበረሰቦች መካከል ይቅር መባባልንና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ እና በመሳሰሉት ሂደቶች ላይ ውጤታማ ለማድረግ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

አሁን ጥያቄው ዜጎችና እና የፖለቲካ ተዋናዮች የሽግግር ፍትህን ውጤታማ በማድረግ ረገድ በመንግስት፣ ማለትም በመደበኛ የፍትህ ተቋማት እና በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ላይ እምነት አላቸው ወይ የሚለው ነው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በሕዝብ ዘንድ ተደጋግመው የሚነሱ እና የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ከመጽደቁ በፊትም አስቸኳይ እርምጃዎችን የሚሹ ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሁለት አጠቃላይ ጥያቄዎች በተሳታፊዎች ተነስተዋል፡-

- በተለያዩ የመንግስት አስተዳደር እርከኖች (ክልሎች፣ ዞኖች) ፣ ባስልጣናት እና በማህበረሰቡ (በተለይም በተጎጂዎች) መካከል፤ እንዲሁም በግጭት ውስጥ ተሳታፊ በነበሩ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል መግባባትን ለማምጣት የሚያስችል መተማመን አለ ወይ? እንዲሁም፤
- በማህበረሰቡ መካከል፤ በፖለቲካ ሃይሎች፣ እንዲሁም በሌሎች ተዋናዮች መካከል የሽግግር ፍትህ ሂደትን በአግባቡ ለመተግበር የሚያስችል በራስ መተማመን በተለይም በሌሎች ላይ እምነት ለማሳደር የሚያስችል ሂደት እንዲኖር ምን እየተሠራ ነው? የሚሉ ናቸው፡፡

የተሰጡ ምክረሀሳቦች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- በመንግሥት ላይ ዕምነትን ሊያጠናክሩ የሚችሉ ጉዳዮን ለይቶ በማውጣት በፍጥነት ወደሥራ መግባት ያስፈልጋል፤
- ከላይ በተገለጸው መልኩ በመንግስት ላይ ወይም በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ እምነት ለማሳደር በቅርቡ ሊዘጋጅ የታሰበው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እስኪጸድቅ ድረስ መጠበቅ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ እንዲያውም የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ እና አቅም በፈቀደ መጠን የህግ የበላይትን በአገራችን ውስጥ እንዲረጋገጥ በአስቸኳይ ከፍተኛ ጥረት መድረግ ይኖርበታል፡፡

### 5.4. አካታችነት

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አዘገጃጀቱም ሆነ አተገባበሩ ሁሉን አካታች በሆነ መልኩ ተሳትፎን ባረጋገጠ ቁጥር ተቀባይነቱም እንዲሁ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ሂደቱም ተደራሽነትን እና አካባቢያዊ ባለቤትነትን ለማረጋገጥ የአመለካከት ብዝሀነትን በማካታተት ሰፊ የማህብረሰብ ተሳትፎን በተለያየ የአስተዳደር እርከኖች ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም ጾታ፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ባህል፣ ብሔር፣ ሃይማኖት፣ የባህል መሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የከተማና የገጠር ኗሪዎች፣ ክልሎች እና ሌሎችም የልዩነት ዓይነቶች በቸልታ የማይታለፉ የልዩ ልዩ ፍላጎቶች ድምጾች ናቸው። በዚህ ረገድ የአፍሪካ ህብረት በ2019 ዓ.ም. ባወጣው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ የአካታችነትን አስፈላጊነት በዚህ መልኩ ገልጾታል፡ “የሽግግር ፍትህ ከሁሉም ወገን እና የህብረተሰብ ክፍል የተውጣጡ የሀገር አቀፍ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ የሚያረጋግጥ የምክክር እና ሁሉን አቀፍ ሂደት ሲሆን፤ በተለይም የተጎጂዎችን ድምጽ እና ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ ትኩረት ማድረግን ይጠይቃል”። ስለሆነም በመብት ጥሰት ተጠያቂ የሆኑትን ለፍርድ ለማቅረብ የተጎዱ ማህበረሰቦች እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በንቃት የሚሳተፉበት አካታች የሆነ ሀገራዊ የፍትህ ሥርዓት ያስፈልጋል፡፡

### 5.5. የስርዓተ-ጾታ ፍትህ

ስለአካታችነት ስናነሳ ከሁሉም ቀድሞ የሚመጣው የስርዓተ ፆታ ጉዳይ ነው፡፡ የሴቶች ተሳትፎ እንደ ተጎጅዎችና ፍትህ ፈላጊዎች ብቻ ሳይሆን እንደ የሽግግር ፍትህ ሂደት ባለቤቶች በተለይም በሠላምና

ዲሞክራሲ ግንባታ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች እንደመሆናቸውም ጭምር ነው፡፡ ሴቶች በቀደሙ ግጭቶችም ሆነ በቅርቡ በተፈጸሙ ግፎች እና ወንጀሎች በከፍተኛ ሁኔታ ተጎድተዋል፡፡ ለምሳሌ በቅርቡ የተካሄደው የሰሜኑ ጦርነት በሰፊው የሚታወቀው ፆታን መሠረት ያደረጉ የተለያዩ ወንጀሎች መፈጸማቸው ምናልባትም በሰብዓዊነት ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ክስ ሲቀርብ እንሰማለን፡፡ የሴቶችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ በተለይም የተጎጅዎችን ድምፅ ለማሰማት በሴቶች ላይ የሚሠሩ የተለያዩ አገር በቀል ሲቪክ ማህበራት በሽግግር ፍትህ ሥርዐቱ ላይ በቀጥታ ተሳትፎ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ተሳትፎአቸው ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን የፈፀሙ ወንጀለኞችን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ፣ የተጎጅዎችን ቁስል ለመጠገን እና የሴቶችን ደህንነትና ተጋላጭነት ከግምት ውስጥ ያስገባ የተቋማዊ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡
ስለሆነም የሽግግር ፍትህ አጠቃላይ ሂደት ውጤታማ እንዲሆን ሴቶች በፖሊሲ ዝግጅትና ትግበራ ላይ ጉልህ የሆነ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

### 5.6. ተጋላጭ የማህረሰብ ክፍሎች

የሽግግር ፍትህ አማራጮችን ለመወሰን እና ተግባራዊ ለማድረግ- ለምሳሌ ክስ ለመመስረት ወይም ይቅርታ ለማድረግ- ተጋላጭ በሆኑ የማህብረሰብ ክፍሎች ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሊደረግ ይገባል፡፡ በተያያዘም በወንጀሉ ሰለባ የሆኑትን የማህበረሰብ ክፍሎች መልሶ የማቋቋም እና ተገቢውን ካሳ የመክፈል አስፈላጊነትን ስናነሳ በቅድሚያ ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት የተጋላጭ ማህበረሰብ ክፍሎች ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ በህፃናት፣ አካልጉዳተኞች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና ሴቶች ላይ ግፍና አሰቃቂ በደል የፈፀሙ ወንጀሎች በህግ ሊጠየቁ ይገባል፤ መጠየቃቸውንም ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

### 5.7. በሽግግር ፍትህ ሂደት የሚካተቱ ግጭቶችን የመለያ መርሆዎች

ለውይይት የቀረበው የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች ሰነድ ዓላማው የተለያዩ አላባዎችን በመጠቀም ከእርስበርስ ግጭቶች በመውጣት በፖለቲካና ዲሞክራሲ ግንባታ ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት ነው፡፡ ይህ ሰነድ የተዘጋጀው የፕሪቶሪያ ስምምነትን ተከትሎ በመሆኑ ሁሉንም በአገሪቱ ውስጥ ተከስተው የነበሩ ወይም ያሉ ግጭቶችን ሁሉ በእኩልነት ለመፍታት ዓላማ አድርጎ የተዘጋጀ ስለመሆኑ ጥርጣሬ ፈጥሯል፡፡ ጥርጣሬውም በፌዴራል መንግሥትና በህወሐት መካከል ተከስቶ በነበረው ጦርነት የደረሰውን ሰብዓዊ መብት ጥሰት ወይም ደግሞ የተፈፀመውን ወንጀል ብቻ ታሳቢ ያደረገ ይመስላል በሚል ነው፡፡ በመሆኑም ስለሽግግር ፍትህ ስንነጋገር ዓላማው በትግራይ ውስጥ ብቻ የተከሰተውን ግጭት ብቻ ለመፍታት ያለመ ነው ወይስ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎችም የተፈጠሩ ግጭቶችን አካትቶ ሁሉን ዓቀፍ የሆነ መፍትሄ ለመስጠት ነው የሚለው ግልጽ መሆን አለበት፡፡
በውይይቱ ጎልቶ የወጣው ሃሳብ አሁን የቀረበው የፖሊሲ አማራጭ በኢትዮጵያ በ1967 እና በ1992 ተሞክሮ እንደነበረውና በአንድ ወገን የተፈጸሙ በደሎችና ወንጀለኞች ላይ ብቻ በማተኮር የአሸናፊዎችን ፍትህ ለማረጋገጥ ጥረት እንዳደረገው ሂደት እንዳይሆን ጥንቃቄ መደረግ አለበት የሚል ነው፡፡

ከዚህ ጋር በታያያዘ የተሰጠው ምክርሀሳብ የሚከተለውን ይመስላል፤-

- በአገሪቱ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን ያስከተሉ ግጭቶችን ማካተት ብቻ ሳይሆን የሽግግር ፍትህ አላባዎችን በተሟላ መልኩ ለመተግበር፤ ፍትህ፣ ሰላምና ዲሞክራሲን ለማረጋገጥ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ፍትሃዊነት፣ እኩልነት ወጥነትና ከአድሎአዊነት በፀዳ መልኩ የመተግበርን አስፈላጊነት መርሆች በግልጽ ያካተተ መሆን እንዳለበት ምክረሀሳብ ተሰጥቷል፡፡

## 6. የሽግግር ፍትህ ዋናዋና ተዋናዮች

በዚህ ክፍል የቀረቡት ጉዳዮች በተሳታፊዎች ሰፋ ያለ አስተያየት የተሰጠባቸው ናቸው፡፡

### 6.1. ኮሚሽኖችና የፍትህ ተቋማት

የሽግግር ፍትህ የትግበራ ሂደት - በተለይም አዳዲስ ተቋማት መገንባት - የሚያደርሰውን ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ ጫና የሲቪል ማህረሰብ ተወካዮች ይገነዘባሉ፡፡ በተለይም በፖሊሲ አማራጮች ላይ ተደጋግሞ እንደተለገጸው አዲስ ኮሚሽን ማቋቋም ወይም ነባር ኮሚሽኖችን እና የፍትህ ተቋማት ማሻሻል ለሽግግር ፍትህ ውጤታማነት አስፈላጊ መሆኑ ተወስቷል፡፡

በሽግግር ፍትህ የሚከናወኑ ተግባራትን የማቀናጀትና የማስተዳደር ተግባር በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡ ፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በተደረጉት ውይይቶች ያሉትን ተቋማት በመጠቀም ወይም አዳዲስ ተቋማት በመመስረት መካከል ያሉ ጥቅሞችና ጉዳቶች በሰፊው ተዳሰዋል፡፡ ነባር ተቋማትን መጠቀም ያለው ኢኮኖሚዊ ጥቅም ግልጽ ቢሆንም፤ ነባር ተቋማትን እንጠቀም ከተባለ ግን የተቋማቱን ነፃነት ማረጋገጥ፤ በተለይም የተቋማቱ ባለሙያዎች ያላቸው ብቃት፣ ቁርጠኝነት፣ ነፃነት እና የወንጀል ሰለባዎችን እና ሌሎች ለፍትህ መረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ አካላትን አሳታፊነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የተቋማቱን ውጤታማት እና ነፃነትን ለማረጋገጥ አንዳንድ የሕግ ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ያለው የይቅርታና ምህረት ማስፈጸሚያ ህግ የሽግግር ሂደቱን ውጤታማነትና ተአማኒነት በሚያረጋግጥ መልኩ መሻሻል ይኖርበታል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ቸል ሊባል የማይገባው ጉዳይ በፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ ላይ በተደጋጋሚ የምክክር ኮሚሽኑን የተለያዩ የሽግግር ፍትህ አላባዎችን ለማስፈፀም እንደ አንድ አማራጭ የቀረበበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የኮሚሽኑ የእስካሁን የሥራ አፈጻጸም፤ አቅም፤ ቅቡልነት፣ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን በማንሳት አዲስ ነጻና ጠንካራ ኮሚሽን የመመሥረት ሃሳብ ትኩረትን ስቧል፡፡ በተጨማሪም ባለፉት አምስት ዓመታት የተመሠረቱና እዚህ ግባ የሚባል ተግባር ሳያከናውኑ የከሰሙ ተቋማት በነባሮቹ ተቋማት ላይ ዕምነት ማጣትን አስከትለዋል፡፡ ስለሆነም እውነትን ለማፈላለግ፣ እርቅን ለማስፈን፣ ይቅርታና ምህረት በህግ አግባብ ለመስጠት እና ተገቢውን ካሳ ለመክፈል አዲስ የእውነትና ዕርቅ ኮሚሽን መመስረት ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

በተጨማሪ የተነሳው ጉዳይ የምርምራና ክስ ሂደትን የሚመለከት ሲሆን የፖሊስ እና ዓቃቤ ህግ ተቋማት አደረጃጀትና ሚና ምን መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ ምክንያቱም በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ እነዚህ ተቋማት በሽግግሩ ሂደት ላይ የሚኖራቸው የተዓማኒነት ችግር ብቻ ሳይሆን በሰብዓዊ መብት ጥሰት ተሳታፊነት ስማቸው የሚነሳ መሆኑም ጭምር ነው፡፡ እንዚህን ተቋማት ሙሉ በሙሉ በአዲስ አወቃቀር መተካት የሚታሰብ ባይሆንም፤ ምርመራና ክስ የማቅረብ ሥራ የሚሰሩ ባለሙያዎች ግን ልዩና ነጻነታቸው በህግ የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

ስለሆነም አቅም ያላቸው፣ ሥነምግባራቸው የተረጋገጠ፣ እምነት የሚጣልባቸው፣ ለፍትህ መረጋገጥ ቁርጠኝነት ያላቸው ባለሙያዎችን ያካተተ ልዩና ነጻ ጽ/ቤት ማቋቋም አስፈላጊ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶችም ቢሆኑ ፖለቲካዊ ገለልተኝነታቸው ጥያቄ ውስጥ የገባ ወይም ወገንተኛ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ እምነት በማጣት ከሚከሰሱት ተቋማት አንዱ ናቸው፡፡ ስለሆነም በሽግግር ፍትህ ሂደት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ልዩ ችሎት በማቋቋም በችሎቱ የሚሰየሙ ዳኞችና ረዳቶቻቸውን አሰያየም ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ገለልተኝነታቸው በተረጋገጥ መልኩ መከናወን አለበት፡፡

ስለሆነም ልዩ የምርምራ ጽ/ቤት እና ልዩ ችሎት በመሰየም ረገድ ሂደቱ ተዓማኒነቱን እንዲያረጋግጥ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ አካዲሚያ (ህግ ትምህርት ቤቶች) ፣ እና ሌሎች በሽግግር ፍትህ ሂደት ላይ ሚና ያላቸውን ነጻ ተቋማትን ተሳታፊ ባደረገ መልኩ ማቋቋም አስፈላጊ ነው፡፡ በአጠቃላይ የፍርድቤት፣ የፖሊስ፣ የዓቃቤ ህግ እና የደህንነት ተቋማትና አባሎቻቸው መሠረታዊ ለውጥ ሳያደረጉ ወይም ማድረጋቸው ሳይረጋገጥ በሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ተገቢ አይሆንም ወይም ስኬቱ ላይ ስጋት ይፈጥራል፡፡ በተያያዘም በቀረበው ምክረ ሀሳብ መሠረት ልዩ ችሎት ወይም ልዩ የምርመራና ክስ ጽ/ቤት ውስጥ እንዲያገለግሉ ለሚመረጡ ባለሙያዎች ምርጫ ዋና መመዘኛዎች - ብቃት፣ ታማኝነት፣ የህዝብ አመኔታ እና የመሳሰሉ መስፈርቶች - ልዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ምክረ ሃሳቦች እንዳሉ ሆኖ የአዲስ ኮሚሽን ምስረታም ሆነ፣ የልዩ የምርመራና ክስ ጽ/ቤት እና ልዩ የፍርድ ቤት ችሎት ቅቡልነት፣ ውጤታማነት እና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ከከፍተኛው አመራር ይጠበቃል፡፡

### 6.2. መንግስት

በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት፣ ዕቅድና አተገባበር ሂደት ውስጥ መንግስት ወሳኝ ተዋናይ ነው፡፡ ያለመንግስት ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት እና ባለቤትነት የሽግግር ፍትህ ሂደት ግቡን ይመታል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ በተለያየ አገራት ልምድ እንደታየው በስልጣን ላይ ያሉ መንግስታት የሽግግር ፍትህን የሚጠቀሙት ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ሳይሆን በህዝብ ዘንድ ታማኝ ሆኖ በመቅረብ ስልጣንን ለማደላደል ነው፡፡ በተያያዘ ሁኔታ በኢትዮጵያ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በአንዳንድ ወገኖች እንደሚቀርበው ከሆነ በቅርቡ  በነበረው የሰሜኑ ጦርነት በወንጀል የሚጠረጠሩ የመንግስት አካላትን አሳልፎ በመስጠት ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የገባውን ቃልዳን ላይጠብቅ ይችላል የሚል ጥርጣሬ አለ፡፡ ይህን ሀሳብ ያጠናክራል የሚል ተደጋጋሚ አስተያየት በተሳታፊዎች የተነሳው ለውይይት በቀረበው የፖሊሲ አማራጭ ሰነድ ውስጥ ክስን እንደአንድ ውጤታማ የሽግግር ፍትህ መሳሪያ ሳይሆን ተጠያቂነትን በማረጋገጥ ረገድ ውጤታማ የመሆን እድሉ የጠበበ በሆነ መልኩ በሰነዱ ላይ መገለጹ እንደ አንድ አስረጅ ቀርቧል፡፡
ስለሆነም መንግስት በማንኛውም መልኩ በሰብዓዊነት ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ላይ ተሳታፊ የሆኑ የመንግስት አካላትንም ሆነ ሌሎችን ለፍርድ ለማቅረብ ያለውን ቁርጠኝነት በማያጠራጥር ሁኔታ ወደፊት በሚወጣው ፖሊሲ ውስጥ በግልጽ በማካተት በማህረሰቡ ዘንድ እምነት ማሳደር ይኖርበታል፡፡

### 6.3. የፖለቲካ ፓርቲዎችና መንግስታዊ ያልሆኑ ተዋናዮች

በቀረበው የፖሊሲ አማራጭ ሰነድ ዝግጅት ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ተዋናዮች በዝግጅት ሂደቱ ላይ ምን ሚና እንደነበራቸው አልተገለጸም፡፡ እነዚህ የተለያዩ ሃይሎች በነበሩ ግጭቶች ውስጥ እንደተባባሪ ወይም እንደ ተጎጂዎች ተለይተው በሽግግር ፍትህ ሂደት ላይ ተሳትፎ እንደሚኖራቸው መገመት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል በትግበራ ሂደቱ ላይ እራሳቸውን ወይም የወንጀል ሰለባ የሆኑ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመወከል ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በዚህ የተሳትፏቸው ሂደት ውስጥ ሊያጋጥም የሚችለው ዋናው ተግዳሮት ጽንፈኝነትና አክራሪ የፖሊቲካ አመለካከት ሲሆን ይህን ለመከላከል የእነሱን ተሳትፎ ከህብረተሰቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ጋር ማመጣጠን የተሻለና ሚዛናዊ አካሄድ ሊሆን ይችላል፡፡

ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የተሰጠው ምክረ ሃሳብ የሚከተለውን ይመስላል፤

- በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት፣ ዕቅድ እና ስኬት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የፖሊቲካ ፓርቲዎችንና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ለመለየትና ሚናቸውን ለመወሰን የሚያስችል ጥናትና የቅድመዝግጅት ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፤
- ይህ የቅድመ ጥናት ሥራ የታጠቁ ሃይሎችን፣ የሚዲያ አካላትን፣ የባህል ተቋማትን ማካተት ውጤታማ ሊያደርገው ይችላል፤
- አገራዊ የፖለቲካ ተሳትፎአቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደ ዲያስፖራ ያሉ ሀይሎችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚያችስል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ሂደቱን የተሟላ ያደርገዋል፡፡

## 6.4. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች

የሽግግር ፍትህ እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የማይነጣጠሉ ከመሆናቸውም በላይ፣ እነዚህ ድርጅቶች ከፖሊሲ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ሙሉ ትግበራ ድረስ ያላቸው ሚና ወሳኝ ነው፡፡ ስለሆነም ይህን ሚናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ወደፊት በሚዘጋጀው ፖሊሲ ውስጥ በግልጽ ተዘርዝሮ መቅረብ አለበት፡፡
በምክክር መድረኮቹ ተደጋግሞ የተገለጸው አስተያየት በአንድ በኩል በፖሊሲ አማራጭ ሰነድ ዝግጅት ላይ ተሳትፎ እንዲኖራቸው አለመደረጉ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሰነዱ ላይ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ሊኖራቸው ስለሚገባ ሚና ትርጉም ባለው መልኩ አለመካተቱ ነው፡፡ ይህን መሠረት በማድረግ በውይይቶቹ ውስጥ አጽንዖት የተሰጠበት ጉዳይ ወደፊት የሚዘጋጀው ፖሊሲ እነኚህ ድርጅቶች ስላላቸውና ስለሚኖራቸው ሚና በግልጽ ማካተት እንዳለበት ነው፡፡ በትግበራ ሂደቱ ላይ የማህበረሰብ ተሳትፎን በማጠናከር ረገድ የሚኖራቸው ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይ በኮሚሽን አመሰራረት፣ የፍትህ ተቋማት ማሻሻያ ሂደት ላይ እና የሰው ሃይል ምልመላና ምደባ ላይ ሰፊ ተሳትፎ ሊኖራቸው እንደሚገባ ትኩረት የተሰጠባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ሊሳተፉባቸው ይችላሉ ተብለው ከተለዩት ጉዳየች መካከል የሚከተሉት ይኙበታል፤
- የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች በማህረሰብ ተሳትፎ- በተለይ በሰብዓዊ ድጋፍ አገልግሎቶች፣ በሰብዓዊ መብት ተሟጋችነት፣ በሰላም ግንባታ ዙሪያ ባላቸው ልምድ መሠረት በሽግግር ፍትህ ተግባራዊነት ላይ ሰፊ ሚና ሊኖራቸው ይገባል፤
- በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት ላይ የማህበረሰብ አቅም ግንባታ ወይም የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ላይ መሳተፍ፤ የማህበረሰቡን ተሳትፎ በማሳደግ ረገድ ተጫማሪ ሚና ይራቸዋል፡፡
- እውነትን በማፈላለግ ሥራ ላይ እምነት የሚጣልባቸውን የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ትርጉም ባለው መልኩ እንዲሳተፉ ማድረግ ጥቅሙ የጎላ ይሆናል፡፡

## 6.5. የአገር በቀል ዕውቀቶችን መጠቀም

የፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ አገር በቀል ዕውቀቶችን ወይም ሌሎች ባህላዊና ሃይማኖታዊ አሰራሮችን ግጭትን በማስወገድ ወይም ዕርቅ በመፍጠር ሂደት ውሰጥ ሊኖራቸው ስለሚገባ ሚና በግልጽ ያስቀመጠው ነገር የለም፡፡ በሰነዱ ላይ በተደረጉት ውይይቶች ጠቅለል ባለ መልኩ ትኩረት የተሰጠው በአገራችን የሚገኙ የተለያዩ ማህረሰቦች የየራሳቸው የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ያላቸው በመሆኑ በሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለውን ገንቢ ሚና ለይቶ ማስቀመጥ አስፈላጊ መሆኑ ነው፡፡ ለዚህ አስተያየት አስረጅ ሆነው የቀረቡት ምክንያቶች በማህበረሰቡ ዘንድ አገር በቀል የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ያላቸው ቅቡልነት፣ የሚከተሉት የአሰራር ሂደት ውስብስብ አለመሆን፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ዘላቂ ሠላም የማምጣት አቅማቸው፣ ማህበረሰቡን ለይቅርታ የማዘጋጀት አቅማቸው፤ እንዲሁም፣ ማህበራዊ ፍትህን ለማረጋገጥ የሚጫወቱት ጉልህ ሚና ናቸው፡

በሌላ በኩል ግን ጥንቃቄ የሚሹ ጉዳዮችም አሉ፡፡ አንዳንድ አገር በቀል እና ባህላዊ ዘዴዎች የሚከተሉት አሰራር እንደ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ካሉ ተጋላጭ ቡድኖች ፍላጎት ጋር የሚቃረኑ ሊሆኑ ይችላሉ፤ አንዱ ባህላዊ አሰራር ከሌላው ጋር የማይጣጣምም ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም አገር በቀል ባህላዊ አሰራሮች አስፈላጊ የሚሆኑበት ጉዳይ እንዳለ ሆኖ፣ እንደ ሰብዓዊ መብቶች ካሉ አለማዓቀፋዊ እሴቶች ጋር የሚቃረን አካሄድ በሚኖራቸው ሁኔታዎች ላይ ግን ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

አገር በቀል የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን በተመለከተ የተሰጡ ምክረ ሃሳቦች፡

- በሰብዓዊነት ላይ የተፈፀሙ ዓለምአቀፍ ወንጀሎች፡ በሕገመንግስቱና በሌሎች የአገሪቱ ህጎች ውስጥ የተካተቱትንና ዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብት መርህ ድንጋጌዎችን ባከበረ መልኩ በዘመናዊው የሽግግር ፍትህ አሰራር መሠረት መታየት ያለባቸው ሲሆን፤ ሌሎች አነስ ያሉ ወንጀሎችን ግን በአገር በቀል ባህላዊ አሠራር ሊታዩ ይችላሉ፡፡
- ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል የሽግግር ፍትህ ከሚከተለው መርህ ጋር በተጣጣመ መልኩ በአንድ ማህበረሰብ ማለትም (አንድ አይነት ባህላዊ ዘዴ በሚከተል) የሚተገበር መሆን ይኖርበታል፡፡ ጉዳዩ የተለያዩ ማህበረሰቦችን የሚመለከት በሆነ ጊዜ ግን ሂደቱ ለመደበኛው የሽግግር ፍትህ ስርዓትና ተቋማት መተው ይኖርበታል፡፡
- ባህላዊ አሠራሮች ተጠያቂነት ከማረጋገጥ አኳያ ጥቅም ላይ የሚውሉ ከሆነ ከሌሎች ዓለም አቀፋዊ እና ሕገ መንግሥታዊ የሰብዓዊ መብት እሴቶች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በቅድሚያ ጥናቶች መደረግ አለባቸው።
- የባህላዊ ግጭት መፍቻ ዘዴዎች አተገባበር ለተጨማሪ አለመግባባቶና ግጭቶች መንስዔ መሆን የለባቸውም፡፡

### 7. **የሽግግር ፍትህ የሚሸፍነው የጊዜ ወሰን-** *ከሰሜኑ ጦርነት ጀምሮ ወይስ በማንኛውም ጊዜ የተከሰቱ ግጭቶችን ባካተተ መልኩ*

የሽግግር ፍትህ ሂደት የሚሸፍነውን የጊዜ መነሻ እና መድረሻ መወሰን አስፈላጊ፣ ነገር ግን ቀላል ያልሆነ ጉዳይ ነው፡፡ የጉዳዩን አሳሳቢነት የአፍሪካ ህብረት ባወጣው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማዕቀፍ ላይ በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ በፖሊሲው ውስጥ የተወሰነ ጊዜን ከመጥቀስ ይልቅ ትኩረት ያደረገው አሰቃቂ ግጭቶችንና ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ወደ ዘላቂ ሰላም፣ ፍትህ እና ዲሞክራሲ የሚደረግ እውነተኛ ሽግግር እንዲሆን ማድረግን ነው፡፡ የመነሻ ጊዜን ለመወሰን ማስረጃና ምስክር የማግኘት ዕድል መኖሩን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የሚሸፍነውን ጊዜ ለመወሰን ስምምነት ይኖራል ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡ አንዳንዶች በቅርቡ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የተካሄደውን ጦርነት በተመለከተ ብቻ ተግባራዊ ይደረግ ሲሉ ሌሎች ደግሞ በጠቅላላው ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ተያይዞ የሚታይ ጉዳይ በመሆኑ ጊዜ እስከፈቀደ ድረስ ወደኋላ ሄዶ ማየት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡ በእነዚህ ሁለት ተቃራኒ ሃሳቦች መካከል ደግሞ ከደርግ መውደቅ ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ማየት፤ ማስረጃና መረጃ ለማግኘት ችግር አይኖርም ሲሉ ሌሎች ደግሞ አገራችን አስከፊ ግጭት ውስጥ ከገባችበት ከ1967 ጀምሮ መሆን አለበት ይላሉ፡፡ ጠንከር ብሎ የወጣው አስተያየት እንደምክንያት ያነሳቸው ጉዳዮች አገራዊ ሁኔታዎችን እና ማስረጃ የማግኘት ዕድልን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል የሚል ነው፡፡ ይህም በአንዳንድ አገራት እንደታየውና ከላይ በተነሱት ምክንያቶች በአንድ የትውልድ ጊዜ ቢወሰን የሽግግር ፍትህ የሚሸፍነው ጊዜ ከ1983 ጀምሮ ያለውን መሆን አለበት የሚል ነው፡፡
የጊዜ ገደብን በተመለከተ የተሰጡ ምክረሃሳቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ከክስ እስከ ይቅርታ ድረስ የሚሸፍነው የሽግግር ፍትህ ሂደት ጊዜን ከመወሰን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡ ስለሆነም ወንጀልን ከምክንያታዊ ጥርጣሬነት በዘለለ በማስረጃና መረጃ የማረጋገጥ ዕድልን፣ የወንጀል ፍትህን ለማስፈን ያሉ አስቻይ ሁኔታዎችን፣ የበደለኝነት ስሜት ከመቅረፍ እና የግጭት መንስዔዎችን ወደ ሰላም ግንባታ ለመቀየር ካሉ ዕድሎች ጋር በማጣመር ጊዜን መወሰን፤
- ተግባራዊ በሚደረጉ የሽግግር ፍትህ አላባዎች ላይ ተመስርቶ የተለያዩ የጊዜ ወሰን የመጠቀም አስፈላጊነትን ማየት፤
- ከላይ በተዘረዘሩት አጠቃላይ መመዘኛዎች ተመርኩዞን ከ1983 በፊት የነበሩ ጉዳዮችን ላይ እውነትን ፍለጋ፣ ዕርቅ እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን በመጠቀም መፍታት፤
- ከ1983 ዓ.ም በኋላ የተከሰቱ ግጭቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ግን በክስ ፍትህን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

## 8. ፌዴራሊዝምና ሕገመንግስታዊ ጉዳዮች

የፌዴራል ስርዓት አንዱ መገለጫ የመንግስት ስልጣን በፌዴራልና በክልሎች መካከል የተከፋፈለ መሆኑ ነው፡፡ የሽግግር ፍትህ ሂደትን የመምራት ጉዳይም ከዚህ የሥልጣን ክፍፍል አንፃር የሚታይ ነው፡፡ አንዱ የሥልጣን ክፍፍል መርህ የፌዴራል መንግስት ስልጣን የሁሉም ክልሎች ጉዳይ ወይም ሁለትና ከሁለት በላይ ክልሎችን ጉዳይ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ የሽግግር ፍትህ ሂደት ሁሉንም ክልሎች እና የማህበረሰብ ክፍሎች የሚመለከት ጉዳይ በመሆኑ የፌዴራል መንግስቱ ፖሊሲ የማውጣትና የማስፈጸም ሃላፊነት አለበት፡፡ ይህ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ አንዳንድ ክልሎች የዕርቅ ኮሚሽን ያቋቋሙ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በማቋቋም ሂደት በመሆናቸው የሽግግር ፍትህ አተገባበር ላይ የፌዴራሉና የክልሎች ተቋማዊ አደረጃጀትና የሥልጣን ግንኙነት ምን መልክ ይኖረዋል የሚለውን ጥያቄ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ክልሎች የሚያቋቁሟቸው ኮሚሽኖችና ሊያካሂዱ የሚያስቡት የሽግግር ሂደት ከፌዴራሊዝሙ መርህ አንጻር ሲታይ በዋናነት ሂደቱና ውጤቱ በአንድ ክልል ብቻ የተወሰነ መሆን ይኖርበታል፡፡ የክልላዊ ግጭትን ከመፍታትና ዕርቅ ከማስፈን ሂደት አንጻር በአንድ ክልል ውስጥ በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ዘንድ ዘላቂ ሰላምን ማስፈን ሊበረታታ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ውሳኔው ወይም ሂደቱ ሌላ ክልልን ወይም የሌላ ክልል ማህበረሰብን የሚመለከተው በተበዳይነትም ይሁን ወይም በጥፋተኝነት የሚፈርጅ አካሄድ ከሆነ የፌዴራል መንግስት ሊከተለው ከሚገባው አካሄድ ጋር ግጭት ይፈጥራል፡፡ ስለሆነም የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት በፌዴራልና በክልሎች ሕገመንግስቱን መሠረት ያደረገ ግልጽና ውጤታማ ውይይት መካሄድ ይኖርበታል፡፡ አስፈላጊ ከሆነም የህግ ማዕቀፍ ሊዘጋጅለት ይገባል፡፡ በተለይ በክልሎች የሚቋቋሙ ተቋማት ከባህላዊ ሥርዓት ጋር ትስስር ይኖራቸዋል ተብሎ ሰለሚገመት በቅድሚያ የተቋማቱን ገለልተኝነት፣ ተቀባይነትና ዘላቂነት በሚያረጋግጥ መልኩ የህግ ማዕቀፍ ሊዘጋጅለት ይገባል፡፡ ስለሆነም የፌዴራልና የክልሎች ስልጣንን በመወሰን ረገድ ወይም መደበኛውን የፍትህ ስርዓት ከባህላዊው ስርዓት ጋር ለማጣጣም በሚያስፈልግበት ጊዜ ሁሉ መመሪያና መርሆዎች የያዙ የህግ ማዕቀፍ በቅድሚያ ማዘጋጀት ከድንገተኛ እና ካልተጠበቁ የሥልጣን ግጭቶች ይጠብቃል፡፡

በውይይቱ የተነሳው ሌላው ጉዳይ በሰነዱ ላይ የሕገመንግስቱን አንቀጽ 28 ለመተርጎም ከተሞከረው ጋር ይያያዛል፡፡ የሕገመንግስቱ አንቀጽ 28 በግልጽ እንደደነገገው "ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለምዓቀፍ ስምምትና በሌሎች የኢትዮጵያ ህጎች በሰው ልጅ የተፈፀሙት ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን፤ የሰው ዘር የማጥፋት፤ ያለፍርድ የሞት ቅጣት ርምጃ የመውሰድ፤ በአስገዳጅ ሰውን መሰወር፤ ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በመፈጸሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም፡፡ በህግ አውጭው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግስት አካል በይቅርታ ወይም በምህረት አይታለፍም፡፡" ይህ አንቀጽ ከዓለምአቀፍ ህጎችና አሰራሮች ጋር ተመሳሳይነት ያለውና በሰብዓዊነት

ላይ በተፈፀሙ ዓለምዓቀፍ ወንጀሎች ላይ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ተግባር ላይ የሚውል ነው፡፡ ነገርግን ሰነዱ ህገመንግስቱን በመተርጎም በሰብእና ላይ በተፈፀሙ ወንጀሎች ዙሪያ ምህረትና ይቅርታ ስለሚሰጥበት ሁኔታ ትንታኔ ያቀርባል፡፡

በኢትዮጵያ ሁኔታ የሽግግር ፍትህ ሂደቱን ውጤታማ ለማድረግ ይቅርታና ምህረት ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ቢያንስ ህገመንግስታዊ ትርጉም ወይም ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 9. ተቋማዊ ማሻሻያ

የሽግግር ፍትሕ ያለፉትን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ለመቅረፍ፣ እንደገና የሰብዓዊ መብት ረገጣ መከሰትን ለመግታት፣ እርቅን ለማጎልበት እና ተጠያቂነት ለማረጋጥ ይጠቅማል። እነኚህን ዓላማዎች ለማሳካት በተለይም ያለፉት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ አሁን በሥራ ላይ ያሉ ተቋማትንና ሰራተኞችን በመጠቀም እንዴት የሽግግር ፍትህ ሂደትን የተሳካ ማድረግ ይቻላል የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ተቋማዊ ሪፎርምን በሶስት ምድብ ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው የሽግግር ፍትህን ተግባራዊ ለማድረግ በሥራ ላይ ያሉ ተቋማትን (የሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና የምክክር ኮሚሽንን) ሪፎርም ስለማድረግ ወይም አዲስ የዕርቀሰላም ኮሚሽን ማቋቋምን ይመለከታል፡፡ የእነኚህ ተቋማትን አቅም መገንባት፣ ግልጽነትን እና ተዓማኒነትን ስለመገንባት ከላይ በተራ ቁጥር 4.1. ላይ የተገለጹ ምክረሃሳቦችን ይመለከታል፡፡ በሁለተኛው ምድብ በሰብዓዊ መብት ረገጣና ግፍ መፈጸም ጋር ተያይዞ የሚነሱ ተቋማትን ይመለከታል፡፡ እነኚህ ተቋማት በቀጥታም ይሆን በተዘዋዋሪ በግጭት ወይም በሰላም ማስከበር ሥራ ላይ ተሳታፊ በመሆናቸው በሽግግር ሂደቱ ላይ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም የደህንነት ተቋማት፣ ፖሊስ፣ ዓቃቤ ህግ፣ በተወሰነ መልክም የዳኝነት አካሉ ሪፎርሙ የሚመለከታቸው ሊሆን ይገባል፡፡ የሽግግር ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን እነዚህን ተቋማት ማሻሻያማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይም እውነት ለማፈላለግ፣ ክስ ለመመስረት፣ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እና የእርቅ ሂደትን ለማከናወን በአጠቃላይ ከግጭት ወደሰላም ግንባታ የሚደረገውን ሂደት የተሳካ ለማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የማሻሻያ ሂደቶች በአጠቃላይ በመንግስት አሰራር ካልታገዙ ውጤታማነታቸው ውስን ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም በሶስተኛው ምድብ የሚነሳው ጉዳይ በመንግስት ተቋማት ውስጥ ሙስና፣ ሌብነት፣ አድሎአዊ አሰራርን በአጠቃላይ ከብልሹ አሰራ የፀዳ የመንግስት አሰራርን ለመገንባት አስፈላጊ የማሻሻያ ሥራ መሠራት ይኖርበታል፡፡ ለሽግግር ሂደቱ መሳካት መደላድል ለመፍጠርና ሰላምና ዲሞክራሲ ለመገንባት ከላይ በሦስት ምድብ የተዘረዘረው ተቋማዊ ማሻሻያ አስፈላጊ ነው፡፡

የተቋማት ማሻሻያ እና የተቋም አቅም ግንባታ ሥራ ለነገ የሚባል ጉዳይ ባለመሆኑ፤ ከላይ የተዘረዘሩትን የተቋማት ሪፎርም ሥራ ከሽግግር ፍትህ ሂደቱ ጋር ብቻ አያይዞ ማየት ወይም ሂደቱ እስኪጀምር ድረስ ማዘግየት ተገቢ አይሆንም፡፡ በተቻለ መጠን በሰብዓዊ ጥሰት ጉዳይ ተሳታፊ ናቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ተቋማት ማሻሻያ እንዲሁም አመራሮች ላይ የለውጥና የአቅም ግንባታ ሥራ መሰራት አለበት፡፡

## 10. የሽግግር ፍትህ ዓለምአቀፋዊነትና የንጽጽር መለኪያ

በምክክሩ ሂደት በርካታ አለምዓቀፋዊ ገጽታዎች ተነስተዋል፡፡ የተለያዩ አገራት ልምድ ከአለምዓቀፍ ማህበረሰብ ሚና አንጻር ለማየት ተሞክሯል፡፡ በኢትዮጵያም በተለይ የአፍሪካ ህብረት፣ አሜሪካ፣

የአውሮፓ ህብረት፣ ልሂቃን እና ሌሎች የሰብዓዊ መብት ተቋማት ሚና ምን ይመስላል በሚል ለማየት ተሞክሯል፡፡ በሌላ በኩል ሉዓላዊነትንና በአንድ አገር የውጭ ጣልቃ ገብነትን የመከላከል አስፈላጊነትንም አመልክቷል፡፡ በውይይቱ ለማየት የተሞከረው የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትን ባስጠበቀ መልኩ እንዴት ከዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ጋር መሥራት የሽግግር ሂደቱን የተሳካ ማድረግ ይቻላል በሚለው ላይ ነው፡፡

ሀ. የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ ገለልተኝነትን ባረጋገጠ መልኩ መጠቀም፤

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትን ባከበረ መልኩ የአለምዓቀፍ ማህበረሰብ በፖሊሲ ዝግጅትና በትግበራ ሂደት ላይ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የልማት አጋር አገሮችና ዓለምአቀፍ ተቋማት የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ይህ ድጋፍ ግን እንደ "ባለሁለት አፍ ሰይፍ" ሆኖ ሊመጣ እንደሚችልም ሊተኮርበት ይገባል፡፡ በአንድ በኩል የሽግግር ፍትህ ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን አገሮች በቀጥታ ወይም በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ወይም በዓለምአቀፍ ድርጅቶች በኩል ሉዓላዊነትን ባከበረ መልኩ የገንዘብና የሙያ ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በዋናነት መንግስት እንዲሁም ሌሎች በሽግግሩ ሂደት ውሰጥ ተሳታፊ የሚሆኑ ሃይሎች በሙሉ የሽግግር ሂደቱን እንዳያደናቅፉና ወደሌላ ዙር ጦርነት እንዳይገቡ ማረጋገጫ የሚሰጡበት ሆኖ ሊቀርብም ይችላል፡፡ ይህ አካሄድ በዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብት ወንጀል መከላከል ላይ ያላቸውን ተሳትፎ የሚያሳይ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል፡፡ በተጫማሪም በሽግግር ሂደቱ ላይ እምነት ለሌላቸው የሀገር ውስጥ ተዋናዮች የዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ተሳትፎ እንደ ሶስተኛ ወገን ዋስትና ሆኖ ሊቀርብ ይችላል፡፡ በአጠቃላይ የሽግግር ሂደቱን ውጤታማና አስፈላጊውን ድጋፍ ከሁሉም ወገኖች ለማግኘት በሚያስችል መልኩ ዓለምአቀፍ ይዘት እንዲኖረው ከማድረጉም በላይ፤ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ተሞክረው እንደከሸፉት ተቋማት እንዳይሆን እድል የሚፈጥር ይሆናል፡፡ ከ2011 ዓ.ም በኋላ የተሞከሩ የለውጥ ሂደቶች አለመሳካት፤ በአንድ በኩል ፍርሃትን የሚፈጥር ቢሆንም፤ በሌላ በኩል ግን ወደሰላምና ዲሞክራሲ የሚደረግ ሽግግር ሆኖ እንዲጠናቀቅ በሙሉ ሃይል ለመስራት መነሳሳትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

ለ. ዓለምዓቀፍ እና ውህድ (ድብልቅ) ፍርድቤቶች እና የአሰራር ዘዴዎች

ይህን በተመለከተ የተለያዩ ምክረሀሳቦችና አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡ አንደኛው ምክረሃሳብ በተወሰኑ ዓለምአቀፍ የሰብኣዊ መብት ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎን በተመለከተ የክስ ሂደትን በዓለምአቀፍ ወይም አገራዊ ፍርድቤቶችን እና የዓለምአቀፉን ስርዓት በማዋሃድ (ድብልቅ) የዳኝነት ሥርዓትን ማስኬድ የሚል ነው፡፡ ጊዜያዊ የዓለምአቀፍ ወይም አፍሪካዊ የወንጀል ክስ ሂደትን የሚያይ ፍርድ ቤትን ማቋቋም የሚለው አማራጭ ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቅ በመሆኑ የሽግግር ሂደቱን አላግባብ ረዥም ጊዜ እንዲወስድ ሊያደርገው ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ዓለምአቀፍ አሰራሩ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ሙሉ በሙሉ ተመራጭ ባይሆንም በይግባኝ የሚቀርቡ ጉዳዮችን እንዲያይ የሚል የተወሰነ አስተያየትም አለ፡፡ ከወጭ አንጻር ተመራጭ ሆኖ የሚቀርበው ውህድ የሆነው የዳኝነት ስርዓት ነው፡፡

በአጠቃላይ፤ ከሉዓላዊነትና ከፋይናንስ አቅም አንጻር ሲታይ ሙሉ በሙሉ አገራዊ ፍርድ ቤቶችን በመጠቀም የዳኝነት ስርዓቱን ማስኬድ ተመራጭ በሆነበት ሁኔታም የዓለምአቀፉን ማህበረሰብ ተሳትፎ በተለያዩ መንገዶች ማካተት ይቻላል፡፡ በተለይም በሽግግሩ ሂደት ተሳታፊ የሆኑ የፖለቲካ ሃይሎች መተማመን እስከሚያዳብሩ ድረስ ተሳትፎውን በተለያየ መንገድ ሊያከናውን ይችላል- ለምሳሌ እውነትን በማፈላለግ፣ መረጃ በማሰባሰብ፣ በዕርቅ ሂደት ታዛቢነት፣ እና በመሳሰሉት መንገዶች ሊሳተፍ ይችላል፡፡

ሐ. የሌሎች አገራት ልምድ

የቀረበው የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጭ ሰነድ በአፍሪካ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ ማዕቀፍ እና የበርካታ ሀገራት ልምድ ላይ የተመሰረተ መሆኑ በአዎንታዊነት የሚታይ ነው፡፡ በአንጻሩ ግን፤ የኢትዮጵያ ውስብስብ እና ውጥንቅጥ የፖለቲካ ሂደት የበለጠ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም፤ ካለፉት የርዕዮተዓለም ፈተናዎች እስከ በርካታ ወቅታዊና የቅርብ ጊዜ የብሄር ግጭቶች፣ የብሄር ውክልና ይገባኛል ጥያቄዎችና ግጭቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባ የሽግግር ፍትህ ሂደት ያስፈልጋል፡፡ ይህም አዳዲስ አቀራረብና ልዩ መፍትሄ ለመሻት ጥረት ማድረግን ይጠይቃል፡፡

## 11. የሽግግር ፍትህ አማራጮች

አጠቃላይ የሽግግር ፍትህ አማራጮችንና ንዑስ አማራጮችን በተመለከተ የሚነሱ በርካታ ተግዳሮቶችና ምክረሀሳቦች በምክክሩ ወቅት ትኩረት አግኝተዋል፡፡ አንዳንዶች ትኩረት ያደረጉት የመክሰስና የተጠያቂነትን አስፈላጊነት የሚያቃልል በሚመስል መልኩ በሰነዱ ውስጥ መገለፁ መንግስት ክስን እንደ አንድ የሽግግር ሂደት አላባ የመጠቀም ፍላጎት ላይ ጥርጣሬ ፈጥሯል በሚል ነው፡፡ ሌሎች ደግሞ የህብረተሰብ ታሪክ፣ ቋንቋ እና የድንበር ይገባኛል ጥያቄዎችን ቅድሚያ በመስጠት ለዘላቂ ሰላምና ልማት ሲባል ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል ይላሉ፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ በአንዳንድ ትኩረት በሚሹ የፖሊሲ አማራጭ ጉዳዮች ላይ እንደሚከተለው ምክረ ሀሳብ ተሰጥቷል፡

### 11.1. እውነትን ማፈላለግ

የኢትዮጵያ ታሪክ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እጅግ አከራካሪና ዋነኛው የግጭት መንስኤ እንደሆነ ተሳታፊዎች ይስማማሉ፡፡ በዚህ ረገድ እውነትን መፈለግ ታሪካዊ ውዝግባችንን ለመፍታት ጥሩ አማራጭ ነው፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ታሪክን ወይም የታሪክ አመለካከቶችን ላልተገባ የፖለቲካ ትርፍ ጥቅም ላይ የማዋል ዝንባሌን አምነን በመቀበል በታሪክ ላይ ለተመሠረቱ አለመግባባቶች እና ግጭቶች ከፍተኛ ትኩረት ልንሰጥ ይገባል፡፡ እነዚህ አለመግባባቶች በአንድ በኩል የራስን ታሪካዊ ጽሁፎች ፍፁም አድርጎ ማቅረብ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሌላውን እስከ መካለስና መካድ ድረስ የሚሄድ ነው፡፡ ስለሆነም ታሪካዊ መረጃዎችና እውነታዎችን መፈለግና ማጣራት መከናወን ያለበት በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል መግባባትና ዕርቅን ለመፍጠር ብቻ ሳይሆን፤ የተጎጅዎችን ጉዳት ለመጠገንም ጭምር መሆን ይኖርበታል፡፡

እውነትን በመፈለግ ሂደት ውስጥ በአንድ በኩል የተለያዩ መንግስታት በግለሰቦች ላይ ያደረሱትን በደልና የሰብዓዊ መብት መጣስ ነቅሶ ማውጣት፤ በሌላ በኩል ደግሞ በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል የተደረጉ ግጭቶችና የደረሱ በደሎችን መለየትንም ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ የዚህ እውነትን የማፈላለግ ዓላማ "ያለፈውን ታሪክ ሊያሳርፍ የሚችለው እውነት ብቻ ነው" እንደሚባለው ነው፡፡

### 11.2. ማካካሻ

በምክክር መድረኩ ተሳታፊዎች ማካካሻን በተለመለከተ ያላቸውን ስጋት በሚከተለው መልኩ ገልጸዋል፡ ፡ ካሳ የሚገባቸው ተጎጅዎች ተለይተው ከታወቁ በኋላ መንግስት ማካካሻ ለመስጠት ቁርጠኝነት ይኖረዋል? ቁርጠኝነት ቢኖረው እንኳን የመክፈል አቅም ይኖረዋል? ለተወሰኑ ጉዳተኞች ካሳ ለመክፈል የሚያስችል ውሳኔ ቢኖር ካሳ የሚገባቸውን ለመለየት የሚያስችል አሰራር፣ ዕቅድ እንዲሁም ሂደቱ አላግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል ለመከላከል የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊነቱ በሰነዱ ላይ እንደተገለጸው መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

በማካካሻ ስርዓት ላይ ትኩረት የሚሹ የተወሰኑ ተግዳሮች በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፡፡

- ማካካሻ የሚገባቸውን ለመለየት ባለፉት ዓመታት የደረሱ ጥፋቶችን እና ጉዳቶችን የሚመለከቱ ሰነዶችን በአግባቡ የመለየትና የማደራጀት ሥራ ችግር ፣
- በአንድ አካባቢ የደረሰን ጉዳት በማካካሻ ለማካተት አስቸጋሪ የሚሆን ሁኔታ ነገር ግን ለማህበረሰቡ የሚኖረው ከፍተኛ ዋጋ እንዴት ሊካተት እንደሚችል ልዩ ትከረት መስጠት ማስፈለጉ (ለምሳሌ በአርበቶ አደሩ አካባቢ በከብቶች ላይ የደረሰን ጉዳት መመዘን) ፣
- በማካካሻ ስርዓቱ ውስጥ ለካሳ የሚሆን ገንዘብ ከመንግስት እና ጥፋት ፈጻሚዎች ለማግኘት ቢታሰብ እንኳን ያለዓለምዓቀፉ ማህበረሰብ ድጋፍ የሚታሰብ አይሆንም፣ ከሱም የሚገኘው ድጋፍ ውስን ሊሆን እንደሚችል በማሰብ በጥንቃቄ መሰራት እንዳለበት፣
- ማካካሻ ይሰጥ ሲባል ያለውን የተገደበ የገንዘብ ዓቅም ከግምት ማስገባት፣ እንዲሁም ካሳ ለሚያስፈልጋቸው በማንና በምን መሥፈርት ካሳ ሊሰጥ ይችላል የሚሉ ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በሚያስፈልገው የህግ ማዕቀፍ ውስጥ የአሠራር መርሆዎች ማለትም ፍትሃዊነት፣ እኩልነት፣ ቅድሚያ የሚሠጠውን መለያ መስፈርት፣ እንዲሁም ሥራው በማን መሰራት እንዳለበት የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ማስቀመጥ፣
- የማካካሻ አሰራርን የሚመለከት የህግ ማአቀፍ ሲዘጋጅና ሲተገበር በተቻለ መጠን የተጎጂዎችን ተሳትፎ ባካተተ መልኩ ቢከናወን የሚሉ ናቸው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ቢኖሩም የማካካሻ እርምጃዎችን በህግ ማዕቀፍ ውስጥ ማካተት ችግሩን ይቀንሳል፡፡ ይህም ግለሰብንና ማህበረሰብን የሚመለከቱ የተለያዩ እርምጃዎችን ለመውሰድ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች ኢንቨስትመንትን ማበረታታትና ድጋፍ የሚሰጥበትን ስርዓት መዘርጋት፡፡ ለተጎጅዎች በመንግስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት በኩል የተለያዩ ድጋፎችን ማድረግ፣ ልዩ የብድር ስርዓት ማዘጋጀት እና የረዥም ጊዜ የበጀት ድጋፍ ለተጎጂ አካባቢዎች የሚሰጥበትን መንገድ መዘርጋት "እንደማካካሻ" ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

## 11.3. ክስ

የሽግግር ስርዓቱ ያለፉትን አሰቃቂ ድርጊቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ፣ ፍትህን ለማረጋገጥ እንጅ ጥፋተኛ ሊሆኑ የሚገባቸውን ላለመክሰስ ወይም በጥቅሉ ይቅር ለማለት አይደለም፡፡ ከሌሎች አገራት ልምድ እንዳየነው እንዲህ ዓይነት ተግዳሮቶች በኢትዮጵያም ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በዚህ ረገድ ወደፊት የሚዘገጀው ፖሊሲ በግልጽ ያለመከሰስ መብትን የሚከላከል ሆኖ መዘጋጀት አለበት፡፡ ምክንያቱም የፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ በወንጀል ክስ ተጠያቂነት የማረጋገጥ አስፈላጊነት ላይ የላላ አቋም የያዘ ይመስላል፡፡ በእርግጥ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ረገጣ ጋር  በተያያዘ የሚደረገው  ምርመራና የክስ ሂደት አስቸጋሪነቱ የታወቀ ነው፡፡ ነገር ግን ፖሊሲው የክስንና የቅጣት አስፈላጊነትን አጽንኦት ባለው መልኩ  ሊገልጽ ይገባል፡፡ ምክንያቱም በከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ረገጣ ተጠያቂ ናቸው ተብሎ የሚገመቱትን ለፍርድ ማቅረብ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ስለሆነ ነው፡፡ የህመንግስቱ አንቀጽ 28 ዓላማም ይህን ማረጋገጥ ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚነሳው ጉዳይ የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡ መንግስት ሂደቱን በብቸኝነት በመቆጣጠር የፈለገውን ለመክሰስ ወይ ላለመክሰስ እንዲሁም ይቅር ለማለት እንዳይችል በፖሊሲው ውስጥ ግልጽ መርሆዎችና የአሰራር ሂደቶች ሊዘረጉ ይገባል፡፡ እንዲህ ዓይነት አሰራር በተቻለ መጠን የፖለቲካና እና የመንግስት ስልጣን የነበራቸውን ተጠርጣሪዎች ሁሉ በህግ መጠየቃቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ከሂደቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን በየጊዜው ግልጽ በሆነ መልኩ ማቅረብ ይርበታል፡፡ ለምሳሌ ምን ያህል ሰዎች በምርምራ ላይ እንደሆኑ፣ ምን ያህሉ ላይ ክስ እንደተመሰረተ፣ እንዲሁም ምን ያህሉ በእርቅና ምህረት ጉዳያቸው እየታየ እንደሆነ ጊዜውን የጠበቀ ሪፖርት ማቅረብ ተአማኒነትን ይገነባል፡፡

## 11.4. ምህረት

ከላይ ባሉት ክፍሎች ተደጋግሞ እንደተነሳው የፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ በአንድ በኩል የወንጀል ክስን በተመለከተ የላላ በሌላ በኩል ደግሞ ምህረትንና ይቅርታን የሚያበረታታ ይመስላል የሚል ነው፡፡ በመሆኑም የምክክሩ ተሳታፊዎች ይቅርታና ምህረት ሊደረግ የሚገባው ለሰላምና ዕርቅ የመጨረሻ አማራጭ ሲሆን እንጅ በደምሳሳው ተጠያቂነትን ለይስሙላ ለመጠቀም ወይም ሙሉ በሙሉ ለመደምሰስ አይደለም፡፡ በተለይም በሰሜኑ ጦርነት (ትግራይ፣ አፋር፣ አማራ) ወቅት ለተፈጸሙ ዓለምዐቀፍ ወንጀሎች ይቅርታ ሊደረግ አይገባም፡፡

## 11.5. ፖሊሲ አማራጭና አተገባበሩን በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች

በፖሊሲ ዝግጅትና ትግበራ ሂደት ውስጥ የሚካተቱ አማራጮችን ለመወሰንና የሽግግር ሂደቱን የተሳካ ለማድረግ ተሳታፊዎች ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል ያሏቸው ዋናዋና ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- **ቅድሚያ መስጠትና ቅደም ተከተል**፤- በአማራጭ ሰነዱ ውስጥ የቀረቡትም ሆነ በዚህ መግለጫ የተሰጡ ምክረሃሳቦች በዋናው ፖሊሲ ውስጥ ቢካተቱ እንኳን በአንድ ጊዜ ተግባራዊ ሊደረጉ ይችላሉ ወይ የሚል ጥያቄ ይነሳል፡፡ በገንዘብ አቅም ማነስ ምክንያት ወይም በሌሎች ምክንያቶች እንደአስፈላጊነቱ ቅደም ተከተልን የሚጠይቁ አካሂዶች አሉ፡፡ ለምሳሌ እውነትን ማፈላለግ ከክስና እርቅ በፊት ቀድሞ ሊመጣ ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህን ለመወሰን በቅድሚያ በተዘጋጀ ዕቅድ ላይ መመስረት ይገባል፡፡
- **የፖሊሲ አማራጮች እንደ የግጭት መንስኤዎች**፤- አንዳንድ የፖሊሲ አማራጮች አላግባብ ጥቅም ላይ ሊውሉ ወይም የግጭት መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ስጋት አለ፡፡ በዚህ ረገድ የሚነሳው ቀድሞ ለተፈፀመ የሙብት ረገጣ መታሰቢያነት ማዘጋጀት አንዳንድ ጊዜ ላልታሰበ ዓላማ ሊውል ይችላል የሚል ነው፡፡ ስለዚህ መታሰቢያን በሚመለከተ በቅድሚያ መግባባት ላይ መድረስ አስፈላጊ ነው፡፡ መታሰቢያ ማቆም ላይ ስምምነት ከተደረሰ መግባባትን ሊፈጥሩ የሚችሉ እንደ ሆስፒታልና ትምህርት ቤቶች መገንባት እንዲሁም፤ ከዚህ በፊት የተዘጋጁ መታሰቢያዎችንም ከሽግግር ፍትህ ዓላማ አንጻር በመመርመር መግባባት ላይ መድረስ አስፈላጊ ነው፡፡
- ***መንስኤዎችን መመርመር***፤- *የፖሊሲ አማራጮችን መለየት እና መተግበር ላይ የግጭት ዋና ዋና መንስኤዎችን በአግባቡ ማጥናትና እና የመፍቻ መሳሪያውንም መለየት ያስፈልጋል፡፡*
- **የማስረጃ አስፈላጊነት**፤- የሽግግር ሂደትን በሚመለከት የተወሰዱ እርምጃዎች ወይም የሚደረስባቸው ውሳኔዎች ሁሉም በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው፡፡

# 12. የማጠቃለያ ምክረ ሀሳቦች

## 12.1. ማጠቃላያ

በአጠቃላይ በግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ ውስጥ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የነበራቸው ተሳትፎ አመርቂ ነበር፡፡ በተለይም እውነተኛ የሽግግር ፍትህ ሂደት እስከተተገበረ ድረስ ያላቻውን ፍላጎትና ቁርጠኝነት ያሳዩ ሲሆን በፖሊሲ፣ ዕቅድ፣ ትግበራ እና አጠቃላይ ስኬት ላይ ያላቸውን ከፍተኛ አቅም አሳይተዋል፡፡ በተያያዘም የግብዓት ማሰባሰቡ ሥራ በአጠቃላይ የሽግግር ፍትህ ጽንሰሃሳብ ላይ በተለይ ደግሞ በኢትዮጵያ ሁኔታ ላይ ግንዛቤ ለመስጠት ተጨማሪ ዕድል ፈጥሯል፡፡ በዚህ ሂደት ስለሽግግር ፍትህ አጠቃላይ ይዘት፣ የመንግስት እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሚና፤ እንዲሁም የሽግግር ሂደቱ ትግበራ ስኬታማ እንዲሆን ስለሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ሰፊ ውይይት ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ

ሂደቱ ውስጥ ተሳታፊዎች በመግለጫው የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የተካተቱት ሃሳቦች እንደተጠበቁ ሆነው በሚከተለው መልኩ ሊጠቃለሉ የሚችሉ ጠቃሚ ምክረሀሳቦችን አስተላልፈዋል፡፡

## 12.2. አጠቃላይ ምክረ ሀሳቦች

ከላይ ባሉት እያንዳንዱ ንዑስ ክፍሎች ውስጥ የተለዩ ምክረሀሳቦች ተሰጥተዋል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የተሰጡት ምክረሀሳቦች በሁለት የተከፈሉ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅትና ትግበራ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሲቪል ማበረሰብ ድርጅቶች በፖሊሲ ዝግጅትና አተገባበር ላይ ስላላቸው ሚና ነው፡፡

የመጀመሪያውን ክፍል በተመለከተ የተሰጡ ምክረሀሳቦች፡-

- የሽግግር ፍትህ አላባዎችን በተሟላ እና ወጥ በሆነ መልኩ ተቀናጅተው የሚተገበሩበት የፖሊሲ አቅጣጫ መከተል ይኖርበታል፡
- የሽግግር ፍትህ ነባር አቀራረቦችን እና እንደ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ያሉ ተቋማትን፣ የህግ እና የፖሊሲ ማሻሻያ፣ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ እና ሌሎች የማሻሻያ ውጥኖችን ማቀናጀት ይኖርበታል።
- መንግስት የሽግግር ፍትህ መተግበር ከመጀመሩ በፊትም ሆነ በትግበራ ወቅት ተጠያቂነት የማረጋገጥን ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፤
- ፖሊሲው በሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት የሚኖራቸውን ሚና በግልጽ ዕውቅናና ፍቃድ መስጠት ያስፈልጋል፤
- የሽግግር ፍትህን ለመተግበር የሚወጡ ህጎች የሲቪል ማሰበረሰብ ድርጅቶችን ጨምሮ ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት ማማከር አለበት፤
- ፖሊሲው መቀረጽ ያለበት መንግስት ፖሊሲው ሊያሳካ የሚፈልገውን ግብ እንዲያከብርና እንዲደግፍ በሚያደርግ መልኩ መሆን አለበት፡፡ እንደ ሲቪል ማህበራት እና የትምህርት ተቋማት ዓይነት ገለልተኛ አካላት ደግሞ ሊቋቋም የታሰበውን ኮሚሽን ቢያንስ በከፊል ቁጥጥር ሊያደርጉበት ይገባል፡፡
- በሽግግር ፍትህ ላይ ከተሞችና አንፃራዊ ሰላም በሆኑ ከተሞች ብቻ ሳይሆን ግጭት በተፈጠረባቸው አካባቢዎች ምክክር መደረግ አለበት፡፡
- የሽግግር ሂደቱን የተሳካ ለማድረግ የሚያስችል ጊዜ እና ቅዕበታዊ ሁኔታን በአግባቡ መያዝ ይገባል፡፡ ስለሆነም የፖሊሲ ዕቅድና ተግባር በከፍተኛ ፍጥነትና ቁርጠኝነት መከናወን አለበት፡፡

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሽግግር ፍትህ ውስጥ ያላቸውን ሚና በተመለከተ ከተሰበሰበው ተጨባጭ መረጃ እና ከሌሎች ሀገራት ልምድ ጥቅም ለማግኘት የሚከተሉት ምክረሃሳቦች ቀርበዋል።

- ፖሊሲውን በማርቀቅ ረገድ የሲቪል ማህበራት የላቀ ተሳትፎ
- በሽግግር ፍትህ ላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተሳትፎን የሚያረጋግጥ የፖሊሲ ሰንድ ማዘጋጀት፤
- ፖሊሲውንና አግባብነት ያላቸውን ህጎች መሠረት በማድረግ በተቋማት ምስረታና በሰው ሃይል ምልመላ ወይም ሹመት ላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በንቃት ማሳተፍ፤
- ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚጠበቀው ከአሁን ጀምሮ በፖሊሲ ዝግጅቱ፣ በሂደቱ እና በትግበራው ወቅት እስከ ፍጻሜው ድረስ፤ የሽግግር ፍትህን በንቃት የማስተዋወቅ፣ የውትወታ ስራ እና ድጋፍ ማድረግ።
- የሽግግር ፍትህ ተቋማትን በአቅም ግንባታ በመደገፍ, ምክር እና ማስረጃ በመስጠት, እና ሌሎች ድጋፎችን በመስጠት ጭምር በንቃት መሳተፍ;
- የሽግግር ፍትህ ስኬታማ እንዲረዳ በትግበራ ወቅት ከታች ወደ ላይ ያለውን አቀራረብ በመጠቀም በተለይ በተለያዩ የሰላም፣ የማህበረሰባዊ መግባባት፣ የሰብአዊ መብትና የልማት ፕሮግራሞች (ለተጠቂዎች የህክምና እና ሌሎች አገልግሎቶችን መስጠትን ጨምሮ) በንቃት ተሳትፎ ማድረግ፤
- የሽግግር ፍትህ ሂደቶችን በአግባቡ መሰነድ, መከታተል እና ሪፖርት ማድረግ;
- ተከታታይ የህዝብ ውይይት እና የግንዛቤ ማስጨበጥ እንቅስቃሴዎችን ማካሄድ፤

- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጠንካራ የሽግግር ፍትህ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጥምረት ማቋቋም እና የተለያዩ የስራ ቡድኖችን ማደራጀትየሽግግር ፍትህ ሂደት ስኬታማ እንዲሆን ለማድረግ ከዓለም አቀፍ ተዋናዮች ጋር በትብብር መስራት
- የሽግግር ፍትህ ውስጥ ተዋንያን አቅም ግንባታ ማካሄድ
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የባለድርሻ አካላትን አቅም ማጎልበት
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ወደፊት የሚፈጸሙ ግፍና ወንጀሎችን ከመከላከል በሚያስችል መልኩ አቅማቸውን ማጠናከር

**Funded by USAID *Feteh* (Justice) Activity in Ethiopia**

*This document was produced and published with the support of the American people through the United States Agency for International Development (USAID). The content and opinions expressed in this document in no way reflect the views of USAID or the United States Government.*